

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጃንዋሪ 1-10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

## እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 11-20፣ እና 21-31/2026

## የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2026


አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


## 1. እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

በጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ በአብዛኛዉ ቀናቶች ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆን በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም አዲግራት 3.5፣ 4.5፣ 4.5፣ 3.5፣ ሐሮማያ 4.0፣ 4.6፣ 2.4፣ -3.4፣ 0.2፣ 1.8፣2.0፣ አለም ከተማ 4.0፣ 3.8፣ 3.4፣ 2.5፣ 3.4፣ 3.2፣ 3.0፣ 4.0፣ አምባ ማሪያም 4.5፣ 4.6፣ በሀር ዳር 4.0፣ 3.8፣ 4.6፣ ባቲ 4.0፣ 3.0፣ 2.0፣ 2.0፣ ቡሂ 4.4፣ 2.0፣ 1.0፣ 3.0፣ 0.2፣ 1.4፣ 1.6፣ ኮምቦልቻ 4.6፣ ደበረ ብርሃን 2.6፣ 3.0፣ 1.6፣ -0.4፣ 0.6፣ 3.8፣ 2.0፣ 3.0፣ ዳንግላ 4.8፣ 4.0፣ 3.5፣ 4.0፣ 4.5፣ ቢሾፍቱ 2.8፣ 2.1፣ 2.2፣ 3.2፣ 2.9፣ 2.5፣ እነዋሪ 4.8፣ 4.5፣ እምድብር 4.6፣ ጅግጅጋ 4.2፣ 3.0፣ 2.5፣ 0.5፣ 1.5፣ 0.5፣ ጅማ 4.4፣ 3.4፣ ማይጨዉ 2.5፣ 4.8፣ 4.6፣ 2.2፣ 2.8፣ መሃል ሜዳ 2.5፣ 4.8፣ 4.6፣ 2.2፣ 2.8፣ ሮቤ 4.3፣ 2.8፣ 0.6፣ 3.0፣ 3.2፣ 2.8፣ ወግል ጤና 3.0፣ 2.5፣ 3.0፣ 2.5፣ 2.0፣ 1.5፣ 2.5፣ ወረኢሉ 3.0፣ ጉዶ በረት 3.5፣ 3.5፣ ዳባት 4.2፣ ኮሶበር 4.1፣ ጨለንቆ 2.1፣ -2.0፣ -2.0፣ -3.0፣ -4.0፣ ቁሉቢ 4.5፣ 3.2፣ 3.0፣ 2.8፣ ጨፌ ዶንሳ 3.7፣ 3.0፣ 3.0፣ ጋሸና 4.2፣ 4.9፣ ዉቅሮ 4.5፣ እንዲሁም መልካ ጀባዱ 4.0 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡




ምስል 1፡ ከጃንዋሪ 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአራት (4) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

በሌላ በኩል በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናቶች ላይ ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ገጽታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፣ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ4 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አማን 17.3፣ 11.7፣ 7.8፣ ብላቴ 15.7፣ ፉኙዶ 4.5፣ ሰዉላ 4.2፣ ቴፒ 11.2፣ ወገልጤና 4.5፣ ቡልቂ 30.8፣ እንዲሁም ጌጫ 14፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ቀላል መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት




ምስል፡2 ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 በ24 ሰዓት ውስዋ ከ4 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ጥቂት የቦረና ዞን፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የዳዋ እና ሊበን ዞኖች ላይ ከ2-10 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

በሌላ በኩል ጥቀቲ ምዕራብ አርሲ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ ዞን፣ ላይ ከ2-37 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 5)፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የጃንዋሪ የመጀመሪያው አሰር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለዉ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የመኸር አብቃይ ለሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛው እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በአንጻራዊ መልኩ ጠንከር ያለ ቅዝቃዜ ተስተዉሏል። ይህም ሁኔታ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች ላይ በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ጎን ነበረው፡ ፡ በሌላ በኩል በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ እርጥበት የሚያገኙት ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ የነበረው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ነበረው(ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው መረብ ጋሽ፣ አባይ፣ ተከዜ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦጋዴን፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል እንዲሁም አይሻ ተፋሰሶች ደረቅ የሁኔታ ስር የነበሩ ሲሆን የላይኛው ባሮ አኮቦ እና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። በመሆኑም ደረቃማው የአየር ሁኔታ ተፅዕኖ ስር የነበሩ ተፋሰሶች የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መቀነስ፣ የተለያዩ የውሀ መያዣዎች የውሀ መጠን ከመቀነስ አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 5)።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


Ethiopian Meteorology Institute

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ የሁለተኛዉ አሥር ቀን የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሰፍኖ የሚታይበትና ከዚሁ ጋር ተያይዞም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጥን ያለዉ ዝናብ ለጥቂት ቀናት ያገኛሉ፡፡


### 2.1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ አስር ቀናት በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚነፍሰው ደረቅ እና ቀዝቃዛ አየር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት ላይ በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ምስል 3)።




ምስል፡3 ከጃንዋሪ 11-20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሶስት (3) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የሚመዘገብባቸው ስፍራዎች

በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቹ የሆኑት የደቡብ እና የደቡብ መስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ደረቅ ሆነዉ ይቆያሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በጥቂት የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የመካለኛው እንዲሁም ሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አንጻራዊ የእርጥበት መጠንና የደመና ሽፋን መጨመር የማስከተል ጥንካሬ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡ ፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናቶች ላይ በጣም አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20/2026
የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

Ethiopian Meteorology Institute

| በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| ኦሮሚያ | የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ እና ቡኖ በደሌ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ እና ሸካ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጉቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጉራጌ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣  ጋሞ፣ ጌዲዮ፣ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን፣ ምስራቅ፣ መከከለኛዉና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ፣ በመካከለኛዉ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩት  ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናቶች ላይ በጣም አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ፡፡

## 2.3 1.3 እ.አ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖረው ደረቃ የእርጥበት ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ ስራዎች ለማከናውን  አመቺ እንደሚሆን ይጠበቃል። በአንጻሩ ግን በተወሰኑ የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ስለሚኖረው የሚኖሩ ስጋቶችን ለመቀነስና መልካም

አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| የምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን፤ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜንና ምስራቅ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ሰሜን ሸዋ፣ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ, በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌዲዮ፣ | አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት ለተዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራትና እድገታቸዉን ለመጨረስ<br>• ለቋሚ ተክሎች ዕድገት እንዲሁም የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል | • የወርጭ መከሰት በመስኖ በሚለሙ አትክልቶችና የፍራፍሬ ተክሎች ላይ መጠነኛ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብ፣ አጠናቆ የመውቃትና የማጓጓዝ ስራዎችን ማከናወን<br>• የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል<br>• ከውርጭ ጋር ተያይዞ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ |

## 2.4 እ.አ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት ጃንዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት በአብዛኛው ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የቀረቡትን የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም አሉታዊ ተፅኖዎች መቀነስ አስፈላጊ ነው።

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘርፍ ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በላይኛ ባሮ አኮቦ፣ በጥቂት መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ እና ስምጥ ሸለቆ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ መጠነኛ የውሃ አቅርቦት መኖር | • በቆላማ አካባቢዎች የንጹ መጠጥ ውሃ እጥረት | • የሚገኘውን ውሃ ከብክለት መጠበቅ<br>• ውሃን ከብክነት በመከላከል በቁጠባ መጠቀም |
| በአብዛኛው አባይ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ በላይኛው ገናሌ ዳዋ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • ወንዞች እና ሌሎች የውሃ አካለት በደራሽ ቆሻሻ አለመበከል | • የወንዞች እንዲሁም በሌሎች የዉሃ አካላት መጠን መቀነስ | • የሚገኘውን መጠነኛ የዝናበ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል<br>• የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |